21ኛ ዓመት ቁጥር 27
21th Year No. 27

ባሕር ዳር ነሐሴ 26 ቀን 2009 ዓ.ም
Bahir Dar, Intercalary 1, 2017

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 51.06 ብር
Unit Price Birr 51.06

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 247/2009 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ ማሻሻያ አዋጅ፣**

## Content

**Proclamation No 247/2017**

**A Proclamation Issued to Revise the Establishment Proclamation of the Rural Roads Construction Agency in the Amhara National Regional state.**

## *አዋጅ ቁጥር 247/2009 ዓ.ም*

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣**

በስራ ላይ ያለውን የክልሉን ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 235/2008 ዓ.ም አንዳንድ ድንጋጌዎች ከክልሉ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ እና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ፣

## Proclamation No 247/2017

**A Proclamation Issued to Revise the Establishment Proclamation of the Rural Roads Construction Agency in the Amhara National Regional state.**

WHERE AS, is has been found necessary to revise some provisions of a Proclamation Issued to provide for the Establishment of the Rural Roads Construction Agency of the Regional Proclamation No 235/2016 inconsistent

በተለይም የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮን ስልጣንና ሃላፊነቶች ከሚዘረዝሩት ድንጋጌዎች ጋር የሚታይባቸውን አለመጣጣም በሚያስተካክል መንገድ መርምሮ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.(1)ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 247/2009 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የክልሉን ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 235/2008 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፦

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሻሽሎ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፦

with the Regional executive bodies Establishment and power and duties determination Proclamation specially with the Road and Transport Bureau's power and responsibilities provisions stipulated under;

NOW, THEREFORE, the Council of Amhara Region in accordance with the power vested in it the under sub-article 3/1/ of Article /49/ of the Revised National Constitution the Region here by issued this Proclamation.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "**The Revised Proclamation of the Rural Roads Construction Agency Establishment Proclamation No 247/2017**."

## 2. Amendment

The issued Proclamation No 235/2016 to provide for the Rural Roads Construction Agency Establishment Proclamation is revised by this Proclamation as follows:

A/ Sub-article (1), Article 2 of this Proclamation is amended and replaced with a stated new sub-article (1) herein under,

ለ/ የአዋጁ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 4 ተተክቷል፦

**ዓላማ**

የኤጀንሲው ዋና ዓላማ በክልሉ ውስጥ በሚገኙት የገጠር አካባቢዎች ደረጃቸውን የጠበቁ የገጠር መንገዶችን በመገንባትና በመጠገን የመንገድ መሠረተ-ልማትን ስርጭትና ፍትሐዊ ተደራሽነት ማረጋገጥነው፡፡

ሐ/ የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (6) በዚህ አዋጅ የተሰረዘ ሲሆን በዚሁ ስረዛ ምክንያት ከንዑስ አንቀጽ (7) እስከ ንዑስ አንቀጽ (10) ድረስ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ከንዑስ አንቀጽ (6) እስከ ንዑስ አንቀጽ (9) ሆነው የኋሊት ተሸጋሽገዋል፡፡

መ/ የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (7) (በዚህ አዋጅ አማካኝነት ንዑስ አንቀጽ (6) እንዲሆን የተደረገው)፣እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

6. ለመንገዶች ግንባታና ጥገና ስራ እንዲሁም ለካምፕና ለቢሮ አገልግሎት፣ ለግንባታ ቁሳቁሶች ማምረቻ፣ ለመሳሪያ ማሳረፊያ፣ ለመዳረሻ መንገዶች እንዲሁም አፈርና ድንጋይ ለማስወገድ የሚያስፈልገውን መሬትና እንደ ድንጋይ፣ አፈር፣ አሸዋና የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች በነፃ ወይም እንደ አግባብነቱ የልማት ስራው ከሚከናወንባቸው አካባቢዎች አስተዳደር አካላት ወይም ከህጋዊ ባለይዞታዎች ጋር በሚደረጉ ስምምነቶች መሰረት በሚፈፀም ክፍያ ሊጠቀም ይችላል፡፡

B/ Article 4 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 4:

**Objective**

The main Objective of the agency is to ensure the distribution and fair accessibility of the road infrastructure by constructing and maintaining of the rural roads that keep their own standards, in rural kebeles of the region.

C/ sub-article (6) of Article 6 of the Proclamation is deleted by this Proclamation and due to this deletion the stipulated provisions from sub-article (7) up to sub-article (10) are re-organized as sub-article( 6) up to sub-article (9) backward.

D/ sub-article (7) of Article 6 of the Proclamation is re-organized as sub-article (6) in accordance with this Proclamation is revised as follows,

6. May use free of charge or disburs in accordance with agreements done with local administration bodies or legal land holders where development work is conducted for plots and such as stone, soil and similar natural resources and quarry substances required for the purpose of construction and maintenance of rural roads as well as for the production of construction materials, storage of equipment, roads of destination and the necessity to eradicate soil and stone.

## 3.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕርዳር**

**ነሐሴ 26 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ገዱ አንዳርጋቸዉ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚደንት**

## 3.Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the official date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional state.

**Done at Bahir Dar,**

**This 1 st Day of Intercalary, 2017**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Regional State.**